# የፍጥረተ ዓለም ታሪክ

## ትምህርት ሁለት

## ጠፍቶ የተገኘው ገነት

(ዘፍ 2፥4 - 3፥24)

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES

Biblical Education. For the World. For Free.

# እናስተዋውቅዎ

የሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር በ1997 ዓ.ም. ተመሠረተ፡፡ ይህ አገልግሎት አትራፊ ያልሆነ ድርጅት ሲሆን፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ  አስተምህሮዎችን ለመላው ዓለም በነጻ ለማዳረስ የተቋቋመ ነው፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያለውን ጤናማ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ - መሠረት ያለው ክርስቲያናዊ የአመራር ስልጠና ፍላጎት ምላሽ ለመስጠት፣ ምንም ዓይነት የስልጠና ግብዓቶች የማግኘት እድል ለሌላቸው ክርስቲያን መሪዎች የሴሚነሪ ሥርዓተ-ትምህርቶችን በማዘጋጀት እናሰራጫለን፡፡ ሰርድ ሚሊኒየም ሚኒስትሪ በመላውም ዓለም ለሚገኙ ክርስቲያን መሪዎችና ፓስተሮች የተመጣጠነ ዋጋ ያለው፣ በደጋፊዎች የሚታገዝ፣ ለተጠቃሚው ምቹ፣ በልዩ ልዩ የመገናኛ ብዙሃን ዘዴዎች የታገዘ ሥርዓተ-ትምህርት በአምስት ቋንቋዎች (በእንግሊዝኛ፣ በስፓኝ፣ በራሺያኛ፣ በማንዳሪን ቻይንኛ እና በአረብኛ) አስተርጎሞ አሰራጭቷል፡፡ ሁሉም ትምህርቶች የተጻፉት፣ የተዘጋጁት እና የታተሙት በአገልግሎቱ ውስጥ ሲሆን በ The History Channel©. In 2009 ካሉት ጋር በቅርፅና በጥራት ተመሳሳይነት አላቸው፡፡ የሰርድ ሚሊኒየም ሥራ ማለትም ጥራት ላለው የማስተማሪያና የአኒሜሽን የቪዲዮ ፕሮዳክሽን ሥራዎቹ ሁለት የቴሊ አዋርድ ሽልማቶችን ተቀብሏል፡፡ የማስተማሪያ ግብዓቶቻችን በዲቪዲ፣ በህትመት፣ በኢንተርኔት ማስተላለፊያ ዘዴዎች፣ በሳተላይት የቴሌቪዥን ስርጭት፣ በራዲዮና በቴሌቪዥን ስርጭቶች ለማቅረብ በሚያስችል መልክ የተቀረፁ ናቸው፡፡

ስለ አገልግሎታችን የበለጠ መረጃ ለማግኘትና እንዴት የአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን እንደምትችሉ ማወቅ ከፈለጋችሁ፣ www.thirdmill.org የተሰኘውን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡፡

## ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር**

ወፍ በረር ዳሰሳ

በገነት

በረከት

መርገም

ከገነት መባረር

መጠነ ቅርፅ

ጅማሬና ፍፃሜ

በመካከል

3. **ቀደምት ትርጉም**

ገነት

መለያ

ቅድስና

ታማኝነት

በገነት

በከነዓን

መዘዞች

ሞት

ህማም

መባረር

4. **ዘመነኛው ተዛምዶ**

ምሥረታ

ጳውሎስ

ማቴዎስ

እድገት

ጳውሎስ

ያዕቆብ

ፍፃሜ

ሮሜ

ራእይ

5. **ማጠቃለያ**

# 1. መግቢያ

እያንዳንዱ ሰው በአንድ ወይም በሌላ ወቅት አንድ ነገር የማጣት ልምምድ አለው ብዬ አስባለሁ:: ምናልባት መጽሐፍ ሊሆን ይችላል:: ምናልባት ደግሞ የቤት ቁልፍ ሊሆን ይችላል:: ስለ እናንተ ባላውቅም፣ እኔ አንድ ነገር ሲጠፋብኝ የማደርገው የመጀመሪያ ነገር እርምጃዎቼን ወደ ኋላ መለስ ብዬ መቃኘት ነው:: ቢያንስ በልቡናዬ፣ ወደፊትና ወደኋላ በመጓዝ የጠፋብኝን ነገር የት እንዳስቀመጥኩት ደረጃ በደረጃ ለማስታወስ እጥራለሁ:: እርምጃዎቼን ከመረመርሁ በኋላ፣ ምን ስህተት እንደፈፀምሁ በጥንቃቄ እመረምራለሁ:: ከዚያም ቁልፎቼን በትክክለኛ ስፍራቸው እንዲቀመጡ አደርጋለሁ መጽሐፎቼም ወደ መደርደሪያቸው ይመለሳሉ:: ስለዚህ ለእኔ የጠፋብኝን ነገር ለማግኘት ውጤታማው መንገድ ተግባሮቼን መለስ ብሎ መቃኘት ነው::

ይህንን ትምህርት "ጠፍቶ የተገኘው ገነት" የሚል ርዕስ ሰጥተነዋል፣ የምናተኩረውም በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 4 እስከ ምዕራፍ 3 ቁጥር 24 ባለው እና በአዳምና በሔዋን ኃጢአት ላይ በሚያተኩረው ታሪክ ላይ ይሆናል:: ሙሴ አዳምና ሔዋን ገነትን ማጣታቸውን የጻፈው እስራኤላውያን ወደ ኋላ መለስ በማለት አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ የፈፀሙትን ስህተት በማስተዋል እንዲቀለብሱት ለማበረታታት እንደሆነ እናያለን:: እስራኤላውያን እንደገና ገነትን የማግኘትን ተስፋ የሚሰንቁት ከዚህ ታሪክ ሲማሩ ብቻ እንደሆነ ሁሉ፣ ሙሴ ለእስራኤል የጻፈው ይህ ማበረታቻ ዛሬም ለእኛ የእግዚአብሔር መልእክት እንደሆነ እናስተውላለን:: ወደ ኋላ መለስ ብለው የአዳምንና የሔዋንን እርምጃዎች በመቃኘት፣ በዚህ ዘመን ያሉ ክርስቲያኖችም ገነትን ማግኘት ይችላሉ::

የዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 ምርመራችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል:: በመጀመሪያ፣ የምንባቡን ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር እንመለከታለን:: ሁለተኛ፣ ሙሴ ለእስራኤል ልጆች ሲጽፍ ለእነዚህ ምዕራፎች አንግቦት የነበረውን ቀደምት ዓላማ በማግኘቱ ላይ እናተኩራለን::  ሦስተኛ ደግሞ፣ ይህንን ምንባብ በሕይወታችን በአግባቡ እንጠቀምበት ዘንድ አዲስ ኪዳን እንዴት እንደሚመራን በመጠየቅ በዘመነኛው ተዛምዶ ላይ እናተኩራለን:: እስኪ በዚህ ምንባብ ስነ-ጽሁፋዊ አወቃቀር እንጀምር::

# 2. ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር

ምንም እንኳ ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 በጣም ረጅምና በርካታ ርዕሶችን የሚዳስስ ቢሆንም፣ አንድ ወጥ የሆነ ትረካ ነው:: ይህንን ምንባብ በትክክል ለመረዳት፣ እነዚህን ሁለት ምዕራፎች እንደ አንድ ስነ-ጽሑፋዊ ቅርፅ ልናተኩርባቸው ይገባል:: በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 ላይ የምናደርገው የስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር ምርመራችን ሁለት ዐቢይ ጉዳዮችን ይዳስሳል፡ በመጀመሪያ፣ የምንባቡን ዐቢይ ክፍልፋዮች በወፍ በረር እንዳስሳለን፤ ሁለተኛ፣ በእነዚህ የተለያዩ ወሳኝ ክፍሎች መካከል ያለውን መመጣጠን በመመልከት ሙሴ ለእስራኤል ሊል የፈለገውን ማዕከላዊ ሃሳብ እንጨብጣለን:: እስኪ አስቀድመን የዘፍጥረትን ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር በወፍ በረር እንመልከት::

### የወፍ በረር ዳሰሳ

በምዕራፍ 2 ቁጥር 4 የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ ከምናገኘው አጠር ያለ ርዕስ ባሻገር፣ እነዚህ ሁለት ምዕራፎች በአራት ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ:: እነዚህም አራት ምዕራፎች በተቀዳሚነት የሚለዩት በርዕስና በገፀ-ባሕርይ ለውጣቸው ነው:: እነዚህን አራት እርከኖች አንድ ባንድ በመቃኘት መሠረታዊ ይዘታቸውን ጠቅለል እናድርገው::

**በገነት ውስጥ**

የመጀመሪያው የታሪካችን ትዕይንት የሚገኘው በምዕራፍ 2 ከቁጥር 4 እስከ 17 ውስጥ ሲሆን፣ በዚያም እግዚአብሔር አዳምን በዔድን ገነት ማስቀመጡን እንመለከታለን፡፡ ጥቅሶቹ የሚጀምሩት በዔድን ገነት አጠቃላይ ገፅታ ሲሆን፣ ምንባቡ እንደሚነግረንም፣ ጠቅላላው ገነት አዳም ሊኖርበትና ሊሠራበት የተመቸ ስፍራ ነበር፡፡ ከዚያም የዚህ ክፍል ትኩረት ወደ አዳም አፈጣጠርና በገነት ውስጥ እንዲያከናውን ወደተሰጠው ተልዕኮ ጠበብ ይላል፡፡ አዳም በእግዚአብሔር ጸጋ አማካይነት ትልቅ ዕድል ተሰጠው፡፡ ገነትን የእግዚአብሔር እንደራሴ ሆኖ ይጠብቅ ነበር፡፡

## በረከት

የትረካችን ሁለተኛ አንጓ ከምዕራፍ 2 ቁጥር 18 እስከ 25 የሚዘልቅ ሲሆን፣ በዚያም የሰው ዘርን "በረከት" እንመለከታለን፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ እግዚአብሔር በአዳም ሕይወት ውስጥ ትልልቅ በረከቶችን መጨመሩን እንመለከታለን፡፡ ይህ ክፍል የሚጀምረው በምዕራፍ 2 ቁጥር 18 የተገለጠውን አዲስ ችግር በማስተዋወቅ ነው፡፡ በዚያም፣ እግዚአብሔር አዳምን አየና እንዲህ አለ፡

> *ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት (ዘፍጥረት 2፡18)፡፡*

የተቀረው የምዕራፍ 2 ቁጥር 18 እስከ 25 ክፍል እግዚአብሔር ለዚህ ችግር መፍትሄ ስለ መስጠቱ ይዘግባል፡፡ አዳም ከእንስሳት መካከል ረዳት ሲፈልግ ነበር በፍፃሜው ግን እግዚአብሔር ሴትን አበጅቶ ወደ አዳም አመጣለት፡፡ በዚህ መንገድ፣ እግዚአብሔር አስቀድሞውኑ ለአዳምና ለሔዋን ፈጥሮት የነበረውን አስደናቂ ፍጥረት ባረከ፡፡

## እርግማን

የትረካችን ሦስተኛው እርከን ምዕራፍ 3 ቁጥር 1 እስከ 21 የሚገኘው ሲሆን፣ በዚያም የሰው ዘርን "እርግማን" እንመለከታለን፡፡ ይህ ክፍል የሚጀምረው በምዕራፍ 3 ቁጥር 1 አዲስ ርዕስና ገፀ-ባሕርይ በማስተዋወቅ ነው፡፡ ያም ፈታኙ እባብ ነው፡፡ ከዚህ አንስቶ እስከ ቁጥር 21 ድረስ ያለው ክፍል የሚያወሳው እባቡ ስላመጣው ፈተና እና ስለ ፈተናው ውጤት ነው፡፡ ሔዋን በእባቡ ወጥመድ ተያዘች ስለዚህም እሷና አዳም ከተከለከለችው ፍሬ በሉ በመለኮት ፍርድ ስርም ወደቁ፡፡

## ከገነት መባረር

የዚህ ምንባብ አራተኛና ገዢ ውቅር የሚገኘው በምዕራፍ 3 ከቁጥር 22 እስከ 24 ውስጥ ሲሆን ይህንንም የሰው ዘር "ከገነት መባረር" የሚል ርእስ ሰጥተነዋል፡፡ ይህ ክፍል በሌላም ወሳኝ የርዕስ ለውጥ ይለያል፡፡ እግዚአብሔር የሕይወትን ዛፍ አስመልክቶ ስለተፈጠረው ችግር ይናገራል፡፡ በምዕራፍ 3 ቁጥር 22 እንዲህ እናነብባለን፡

> *አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፣ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር (ዘፍጥረት 3፡22)*

አዳም ከፍሬዋ የመብላቱን ችግር ለመጋፈጥ፣ እግዚአብሔር አዳምን ከገነት አባረረውና የገነትን ደጅ ይጠብቁ ዘንድ ኪሩቤልንና የምትገለባበጠውን ሰይፍ አስቀመጠ፡፡ ከዚያን ጊዜ አንስቶ፣ የሰው ዘር ከእግዚአብሔር የቀጥታ ጣልቃ ገብነት ውጪ ወደ ገነት ተመልሶ መግባት የሚችልበትን ዕድል ተነጠቀ፡፡

## መጠነ ልክ

የዚህን ምንባብ አራት ዐቢይ ክፍልፋዮች በልቡናችን ይዘን፣ አሁን ደግሞ በዘፍጥረት ምእራፍ 2 እና 3 ውስጥ ይህ ምንባብ የሚያመለክተውን መጠነ ልክ እንቃኝ፡፡ በዚህ ምንባብ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ውቅረ-ነገሮችን ጎን ለጎን በማስቀመጥ፣ ሙሴ የትረካውን ማእከላዊ ዓላማ ይገልጣል፡፡ የዚህን ትረካ መጠነ ልክ ለመመርመር፣ እስቀድመን በምንባቡ ጅማሬና ፍፃሜ ላይ የምንመለከተውን ምጥጥን እንቃኝ፡፡ ቀጥለን ደግሞ በታሪኩ መካከል የሚገኙትን ሁለት ክፍሎች መጠነ ልክ እንቃኝ፡፡ በመጀመሪያ የምንባቡን ጅማሬና ፍፃሜ እንይ፡፡

## አጀማመርና አጨራረስ

እንደምንመለከተው፣ ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 4 እስከ 17 እና ምዕራፍ 3 ከቁጥር 22 እስከ 24 ቢያንስ በሦስት ወሳኝ መንገዶች አንዳቸው ከሌላቸው ጋር ጉልህ ልዩነት አላቸው፡፡

የመጀመሪያው ልዩነት የስፍራ ነው፡፡ ታሪኩ የሚጀምረው እግዚአብሔር አዳምን በዔድን ገነት ባስቀመጠበት በምዕራፍ 2 ቁጥር 7 ነው፡፡ አዳም ይኖርና ይሠራ የነበረው የተሟላ መለኮታዊ በረከት ባለበት ስፍራ ነበር፡፡ አስደናቂ የአትክልት ስፍራ፣ የሕይወት ውሃ፣ ብርቅ ብረቶችና እና ድንጋዮች ዙሪያውን ከብበውት ነበር፡፡ በተቃራኒው ደግሞ፣ ትረካው የሚደመደመው በምዕራፍ 3 ቁጥር 24 እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከገነት ሲያስወጣቸው ነው፡፡ ይህ መልክዓ-ምድራዊ ተቃርኖ በዚህ ምድር የሰው ዘር ለመኖር የሚጓጓለት ስፍራ የዔድን ገነት ብቻ መሆኑን ግልፅ ያደርግልናል፡፡

በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሚገኘው ሁለተኛው የትኩረት ልዩነት በገነት ውስጥ የሚገኙት ዛፎች ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ምዕራፍ 2 ከቁጥር 4 እስከ 17 ሁለት ዛፎችን ማለትም የሕይወትን ዛፍና መልካምንና ክፉን የምታስታውቀውን ዛፍ ቢጠቅስም፣ ወደ ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 ስንመጣ ግን ትኩረታችን በአንድ ዛፍ ላይ ብቻ ይሆናል፣ እርሱም የእውቀት ዛፍ ነው፡፡ ይህ ዛፍ የሰው ዘር መልካሙንና ክፉውን የሚያውቅበትን ኃይል ይዟል፡፡ ከዚያ በፊት ዐይተው የማያውቁትን ነገር ማየት ይችሉ ዘንድ ዐይናቸውን ይከፍታል፡፡

በተቃራኒው፣ በምዕራፍ 3 ከቁጥር 22 እስከ 24 በሚገኘው በትረካው ማብቂያ ላይ እግዚአብሔር ከዚያ በኋላ መልካሙንና ክፉውን ስለምታስታወቀው ዛፍ ግድ እንደማይለው፣ ግድ የሚለው ስለ ሕይወት ዛፍ እንደሆነ እናያለን፡፡ ይህች ዛፍ ለሰው የዘላለምን ሕይወት የምታስገኝ ናት፡፡ እግዚአብሔር ግን አዳምን በማባረር ወደዚህ ዛፍ እንዳይቀርብ አደረገው፡፡ እግዚአብሔር በሌላ መንገድ ቃል ኪዳኑን እስካላደሰ ድረስ የሰው ዘር በአንድ ወቅት በነፃ አግኝቶት የነበረውን ገነትንና በውስጥዋ የሚገኝ በረከትን ሁሉ የመጠቀም ዕድል ያጣ መሆኑን ይህ ተቃርኖ ያመለክተናል፡፡

በትረካችን ጅማሬና ፍፃሜ ውስጥ የምንመለከተው ሦስተኛው ተቃርኖ በሰው ዘር ተልዕኮ ውስጥ የሚገኘው ነው፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 15 ውስጥ የሚገኘው የመጀመሪያ ዘገባ የሚያሳየን አዳም በተባረከችው ገነት ውስጥ ያለ ስቃይና ችግር እንዲሠራ ተልዕኮ የተሰጠው መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም፣ በምዕራፍ 3 ቁጥር 23 ውስጥ፣ እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ከገነት አባረራቸው ከገነትም ውጪ በድካምና በጥረት እንዲኖሩ ረገማቸው፡፡ ይህም ተቃርኖ በታሪኩ ውስጥ ወሳኝ የሆነውን አመለካከት ያቀርብልናል፡፡ የሰው ዘር የገነትን ድንቅ ሕይወት መነጠቁ ብቻ ሳይሆን፣ ከገነት ውጪ በሚቆይበት ዘመኑ ሁሉ በድካም ይኖር ዘንድም ተረገመ፡፡

በምዕራፍ 2 እና 3 መከፈቻና መዝጊያ ውስጥ የተገለጡ እነዚህ ሦስት ተቃርኖዎች ወደዚህ ትረካ ወሳኝ ገፅታ ትኩረታችንን ይስቡታል፡፡ በጥንት ዘመን በሰው ዘር ሁኔታ ላይ ስለመጣው ዐቢይ ለውጥ ሙሴ ይጽፋል፡፡ የሰው ዘር በገነት ውስጥ እንዲኖር እግዚአብሔር አስቀድሞ ወስኖለት ነበር፣ የአዳምና የሔዋን በደል ግን በችግርና በመከራ እንዲከበቡ አደረጋቸው፣ የዘላለምን ሕይወት ከሚሰጥ ዛፍም ለያቸው፡፡ እንግዲህ እንደምንመለከተው፣ እነዚህ ተቃርኖዎች በሙሴ መሪነት ወደ ተስፋዪቱ ምድር ይጓዙ የነበሩ እስራኤላውያንን ስለ ነበሩበት ሁኔታ በቀጥታ ይናገሯቸዋል፡፡ እስራኤላውያን በግብፅ ጨካኝ አገዛዝ ውስጥ ይሰቃዩ በነበሩባቸው ዓመታት ከገነት እጅግ በራቀ ሕይወት ውስጥ ነበሩ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በገነት ውስጥ ያፈስስ የነበረውን በረከት ወደሚያገኙበት ስፍራ ሊመለሱ ይገባቸው ነበር፡፡

## መካከለኛ ክፍሎች

የታሪኩን ውጨኛ ክፍሎች መጠነ ልክ በልቡናችን ይዘን፣ ወደ ታሪኩ መካከለኛ ክፍል መሸጋገር ይገባናል፣ ያም ምዕራፍ 2 ከቁጥር 18 እስከ 25 ያለውና ምዕራፍ 3 ከቁጥር 1 እስከ 21 ያለው ነው፡፡ እነዚህ ሁለት መካከለኛ ክፍሎች በጅማሬውና በፍፃሜው መካከል ያለውን ክፍተት የሚሞሉ ሲሆን፣ ቢያንስ በሦስት መንገዶች የራሳቸውን የመጠነ ልክ ተቃርኖ ያመለክታሉ፡፡

የመጀመሪያው ተቃርኖ በሰው ዘርና በእግዚአብሔር ግንኙነት ላይ ያተኩራል፡፡ በሁለተኛው እርከን ውስጥ በአዳምና በእግዚአብሔር መካከል የሰመረ ግንኙነት እንመለከታለን፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 18 ውስጥ እግዚአብሔር ስለ አዳም ግድ ብሎት የምትመቸውን ረዳት ሔዋንን ወደ እርሱ ያመጣለታል፡፡ በዚህ ስፍራ የተቀመጠው ምስል እግዚአብሔርና አዳም ስምም እና ሰላም የነበሩ መሆኑን ያሳያል፡፡ ሆኖም፣ የትረካው ሦስተኛ ክፍል በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረው ስምምነት መበላሸቱን ይናገራል፡፡ በምዕራፍ 3 ቁጥር 8 ውስጥ አዳምና ሔዋን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ይተላለፋሉ ራሳቸውንም ከእግዚአብሔር ለመሰወር ይጥራሉ፣ እግዚአብሔርም አዳምንና ሔዋንን በቁጣ ይናገራቸዋል፡፡

ሁለተኛው ተቃርኖ ደግሞ የሰው ዘር የእርስ በርስ ግንኙነት ነው፡፡ የምዕራፍ 2 ከቁጥር 18 እስከ 25 ሁለተኛ እርከን የሚያሳየን አዳምና ሔዋን በፍፁም ደስታ ውስጥ እንደነበሩ ነው፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 23 አዳም አስደናቂ የፍቅር ቅኔ ይቀኛል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን አዳም “ይህች አጥንት ከአጥንቴ ሥጋም ከሥጋዬ ናት” በማለት ሲናገር ሁለቱም ራቁታቸውን ነበሩ አይተፋፈሩም ነበር ተብሎም ተጽፏል፡፡ በተቃራኒው ግን በምዕራፍ 3 ቁጥር 16 እግዚአብሔር ይህንን ግንኙነት ሲረግመውና በወንዱና በሴቲቱ መካከል ጠብ ሲፈጠር እናያለን፡፡ ሴትም ፈቃዷ ወደ ባሏ ይሆናል እርሱም ይገዛታል፡፡ የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት

ብቻ ሳይሆን የእርስ በርሳቸውንም እንዳወከባቸው እነዚህ ቃላት ያስረዳሉ፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮም፣ የሰው ዘር ግንኙነት በችግሮችና በትግሎች የተሞላ ሆነ፡፡

ሦስተኛው ተቃርኖ የተገለጠው በሰው ዘርና በክፉ መካከል ባለው ግንኙነት ነው፡፡ በሁለተኛው እርከን ላይ ክፉ በትዕይንቱ ውስጥ አልነበረም፡፡ አዳምና ሔዋን ንፁህና ከክፋት የራቁ ነበሩ፡፡ በሦስተኛው እርከን ግን፣ የሰው ዘር በእባቡ ወጥመድ ተያዘ ከክፉውም ጋር ለዘመናት ወደሚዘልቅ ትግል ውስጥ ገባ፡፡ በምዕራፍ 3 ቁጥር 15 ውስጥ የሔዋን ዘር እባቡን ድል እንደሚነሳ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠ፣ ሆኖም አዳምና ሔዋን የእጅ በእጅ ድል አልተሰጣቸውም፡፡

እነዚህ በሁለተኛውና በሦስተኛው አንጓ መካከል ያሉ የትረካው ተቃርኖዎች ሙሴ ትረካውን ሲፅፍ ግድ ይሰኝባቸው የነበሩ ነገሮችን እንድናስተውል ያግዙናል፡፡ ሙሴ ስለ አዳምና ሔዋን የጻፈው ከእስራኤል ልምምድ ጋር በተገናኘ መልኩ ነበር፡፡ ኃጢአት የእስራኤልን ሕይወት ማፈራረስና ማጥፋቱን ቀጠለ፡፡ የህዝቡን ከእግዚአብሔርና ከእርስ በርስ ጋር የነበረ ግንኙነት አወደመ፣ ከዚህም ባሻገር፣ በየዕለቱ የሚገጥማቸው ፈተና ልክ እንደ አዳምና ሔዋን ሁሉ እስራኤላውያንም እግዚአብሔር ህዝቡን ከክፋት የሚታደግበትንና ድል የሚያቀዳጅበትን ያንን ቀን መጠበቅ እንዳለባቸው ሙሴን ያሳስበው ነበር፡፡

የዚህን ጽሑፍ ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀር በልቡናችን ይዘን፣ የዚህን ምንባብ ቀደምት ትርጉም ወደ መፈለጉ እንሸጋገራለን፡፡ የሰውን ዘር ከእግዚአብሔር ገነት መባረር ሙሴ ለምን ጻፈ? እስራኤልን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሲመራ ያስተላለፈላቸው መልእክት ምን ነበር?

# 3. ቀደምት ትርጉም

እንግዲህ፣ በመሠረታዊ ደረጃ በእርግጠኝነት ለመናገር፣ ሙሴ ይህንን ትረካ የጻፈው ለሚመራቸው ለእስራኤላውያን ጠቅለል ያሉ ነገረ-መለኮታዊ መሪ ሃሳቦችን ሊያስተምራቸው ነበር፡፡ ስለ ኃጢአት ምንጭ፣ ባህርይና በዓለም ላይ ስላመጣው ዳፋ ብዙ ነግሯቸዋል እነዚያም በጣም ወሳኝ መሪ ሃሳቦች ነበሩ፡፡ ሆኖም፣ ቀደም ባለው ትምህርት እንዳየነው፣ ሙሴ የፍጥረተ ዓለምን ታሪክ የጻፈው ለእስራኤል ስለ ጥቅል ታሪካዊና ነገረ-መለኮታዊ ጉዳዮች መረጃ ለማቀበል ብቻ አልነበረም፡፡ ይልቁኑ፣ እንደ ብዙዎቹ የጥንት ፀሐፍት፣ ሙሴ የፍጥረተ ዓለም ታሪኩን የጻፈው ለህዝቡ ስለ ወቅታዊው ሃይማኖታዊና ማኅበራዊ ፕሮግራሞች፣ በዋናነትም፣ ከግብፅ ስለመውጣትና ወደ ከነዓን ስለ መጓዝ ተግባራዊ መመሪያ ለመስጠት ነበር፡፡

ሙሴ የጥንት ገነትንና የእስራኤልን የከነዓን ድል እንዴት እንዳስተሳሰረው ለማየት፣ የእርሱን ታሪክ ውቅር በሦስት መንገዶች እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ሙሴ ስለ ኤድን ገነት የሰጠው መግለጫ፤ ሁለተኛ፣ ከአዳምና ከሔዋን ይጠበቅባቸው ስለነበረው ታማኝነት የሰጠውን ትኩረት እና ሦስተኛ፣ በአዳምና በሔዋን ላይ ስለ ወደቀው እርግማን የሰጠውን ስዕላዊ መግለጫ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን ሙሴ ስለ ዔድን ገነት የሰጠውን መግለጫ እንመልከት፡፡

### ገነት

ሙሴ ስለ ዔድን ገነት የሰጠው መግለጫ ውስብስብና በዚህ ዘመን የምንኖር ሰዎች ላሉን ጥያቄዎች ምላሽ ልናገኝላቸው የማንችል ናቸው፡፡ ሆኖም፣ የሙሴን አቀራረብ ማዕከላዊ ሃሳብ መጨበጥ

እንችላለን፡፡ እንደምንመለከተው፣ ሙሴ የዔድንን ገነት የገለጠው ከተስፋፉቱ ምድር ጋር በማገናኘት ነው፡፡ ከሙሴ አተያይ አንፃር፣ በእርሱ ዘመን እስራኤልን እየመራ የወሰደበት ምድር ገነት ብለን የምንጠራት ጥንታዊቷ ምድር በእውነት የነበረችበት ነበር፡፡

የዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 በርካታ ገፅታዎች እስራኤል ከነዓንን ከዔድን ጋር እንዲያገናኙ ሙሴ ፍላጎት እንደነበረው በግልፅ ያስቀምጣሉ፡፡ ሁለቱ ግን በተለየ መንገድ ወሳኝ ናቸው፡፡ እነርሱም፡- በመጀመሪያ፣ የዔድን መለያ፤ ሁለተኛ፣ የገነት ቅድስና ናቸው፡፡ አስቀድመን የዔድንን መለያ እንመልከት፡፡

## *መለያ*

በዘፍጥረት 2፡10-14 እንዲህ እናነብባለን፡

> *ወንዝም ገነትን ያጠጣ ዘንድ ከዔድን ይወጣ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ይከፈል ነበር፡፡ የአንደኛው ወንዝ ስም ፊሶን ነው፤ እርሱም ወርቅ የሚገኝበትን የኤውላጥን ምድር ይከብባል፤ የዚያም ምድር ወርቅ ጥሩ ነው፤ … የሁለተኛው ወንዝ ስም ጤግሮስ ነው፤ እርሱም በአሦር ምሥራቅ የሚሄድ ነው፡፡ አራተኛውም ወንዝ ኤፍራጥስ ነው፡፡ (ዘፍጥረት 2 ፡10-14)*

ከዔድን የሚወጣው አንዱ ወንዝ ለአራት እንደሚከፈል ሙሴ ይጽፋል፡፡ እነዚህም አራት ወንዞች ፊሶን፣ ጊዮን፣ ጤግሮስ እና ኤፍራጥስ ናቸው፡፡ ከዔድን የሚወጣው አንዱ ማዕከላዊ ወንዝ እነዚህን አራቱን ይመግባል፡፡ የእነርሱ ማዕከላዊ ምንጭ እርሱ ነው፡፡

በዚህ ስፍራ ሙሴ የሰጠውን መግለጫ ስንመረምር፣ ከዓለም ጅማሬ አንስቶ እስካሁን ድረስ በጠቅላላው የፕላኔታችን ታሪክ ውስጥ በርካታ መልክዓ ምድራዊ ለውጦች የተካሄዱ መሆኑን ልብ ማለት ይገባናል፡፡ በሙሴ ዘመን እንኳን እነዚህን አራት ወንዞች የሚመግብ አንድ ወንዝ አልነበረም፡፡ ቅዱሳት መጻሕፍትም እንደሚያስተምሩን ይህ የወንዞች ምንጭ የሚገለጠው በዘመን ፍፃሜ ላይ ነው፡፡ ሆኖም፣ ሙሴ ከአንዱ ምንጭ ስለሚገኙ ስለ እነዚህ አራት ወንዞች ያቀረበልን ማጣቀሻ ገነት የምትገኝበትን አድራሻ ምስሉን እንድናገኘው ይረዳናል፡፡

በምዕራፍ 2 ቁጥር 14 የተጠቀሱት ጤግሮስና ኤፍራጥስ በዘመናችንም ከሚጠቀሱት የጤግሮስና የኤፍራጥስ ወንዞች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ የዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ እነዚህ ወንዞች ያስቀመጠው መግለጫ በባቢሎናውያኑ ጥንታዊ እምነቶች ጥናት መሠረት ኤድን ምትገኘው በሜሶፖታሚያ ግዛት የመሆኑን እሳቤ የሚያረጋግጥ መሆኑን ዘመናውያኑ ትርጉሞች ያፀናሉ፡፡ በባቢሎናውያን ቋንቋ፣ *Edin* ማለት "ጠፍጣፋ" ወይም "ባዶ ጠፍጣፋ መሬት" ማለት ሲሆን፣ አባባሉም ለታችኛው ጤግሮስ-ኤፍራጥስ አካባቢ የሚስማማ ነው፡፡ ሆኖም፣ በዕብራይስጥ፣ *eden* ማለት "ጠፍጣፋ" ማለት አይደለም፤ "ደስ የሚያሰኝ" ወይም "አስደሳች ስፍራ" ማለት ነው፡፡ ስለዚህ፣ ሙሴ የባቢሎናውያንን ቃል በፍፁም አልተጠቀመም፡፡ እርሱ የተጠቀመው ድምፁ ባቢሎናውያን ለዔድን ከሚጠቀሙበት ቃል ጋር ተመሳሳይ የሆነውን፣ ስለ ስፍራው ያዘለው ጽንሰ-ሃሳብ ግን የተለየ የሆነውን የእብራይስጥ ቃል ነው፡፡ እንዲያውም፣ ዔድን በሜሶፖታሚያ ግዛት የተወሰነ እንዳልሆነ የዘፍጥረት ዘገባ በግልፅ አስቀምጦታል፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 10 እንደምንመለከተው፣

ጤግሮስና ኤፍራጥስ በኤድን ከሚገኝ አንድ ታላቅ ወንዝ ይመነጫሉ፡፡ በቁጥር 10 እንዲህ ይነበባል፡

*ወንዝም ገነተን ያጠጣ ዘንድ ከዔድን ይወጣ ነበር፤ ከዚያም ለአራት ይከፈል ነበር፡፡ (ዘፍጥረት 2፡10)*

ይህ ምንባብ የሚያስተምረን የዔድን ወንዝ የጤግሮስና የኤፍራጥስን ወንዞች እንደሚመግብ ነው እንጂ፣ ዔድን በጤግሮስና በኤፍራጥስ የተወሰነ መሆኑን አይደለም፡፡ ሙሴ ጤግሮስንና ኤፍራጥስን የጠቀሰው ስለ ምሥራቃዊው የዔድን ድንበር ጥቅል መግለጫ ለመስጠት ነው፡፡ በምሥራቅ የሚገኙት ታላላቆቹ ወንዞች የኤድንን ግዛት ምሥራቃዊ ወሰን ያሳያል፡፡

ይህ አመለካከት በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 በተጠቀሱ ሌሎች ወንዞች አድራሻም ተረጋግጧል፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 11 እስከ 13፣ ሙሴ ሌሎች መንታ ወንዞችን ይጠቅሳል፡፡ የዔድን ወንዝ ፊሶንን እንደሚመግብ፣ ያም የኤውላጥን ምድር እንደሚከብብ ደግሞም የጊዮንንም ወንዝ እንደሚመግብና ያም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ እንደሚከብብ ይናገራል፡፡ በብሉይ ኪዳን የኤውላጥ እና የኢትዮጵያ ምድሮች ከግብጽ ግዛቶች ጋር ተያይዘው ይቀርባሉ፡፡ ሙሴ እንዚህን ወንዞች ከትልቁ የዐባይ ወንዝ ጋር አያይዞ ስለ መጥቀሱ በእርግጠኝነት መናገር አንችልም፡፡ ስለዚህ ሙሴ እያመለከተ ያለው የዔድን ምዕራባዊ ወሰን የሆነውን የሰሜናዊ ግብጽ ግዛት ነው ማለት ይሻላል፡፡

ስለዚህ ሙሴ ስለ ዔድን ሲናገር ስለ ትንሽ ስፍራ አለመናገሩን እናያለን፡፡ ከጤግሮስና ከኤፍራጥስ እስከ ግብጽ ድንበር ድረስ የሚዘልቅ ሰፊ ስፍራ ይሆንና ዛሬ ለም የማጭድ ቅርፅ ምድር ብለን የምንጠራውን ሁሉ ያካትታል፡፡ በዚህ ደስ የሚያሰኝ ስፍራ ልዩ ገነት ነበር፣ ያም የዔድን ገነት፣ የታላቁ የዔድን ግዛት ማዕከላዊ ስፍራ ነው፡፡

ሙሴ ዔድንን ከለምለሚ ምድር ጋር የማመሳሰሉ ነገር ያን ያህልም ወሳኝ መስሎ አይታይም፡፡ እንደ እውነታው፣ ሙሴ የዘፍጥረትን መጽሐፍ ለጻፈላቸው ለእስራኤላውያን ግን የዔድንን ወሳኝነት መገንዘብ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ በዘፍጥረት መጽሐፍ በሌላ ስፍራ፣ ሙሴ እንደገና ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 በመጥቀስ የዔድን ምድር፣ ለምለሚ ምድር፣ ለእስራኤል ተስፋ የተገባችው፣ እርሱም እስኤልን እየመራ የወሰደባት ምድር መሆኗን ለእስራኤል ያስተምራል፡፡ ይህ አመለካከት ይበልጥ ግልፅ የሚሆነው በዘፍጥረት ምዕራፍ 15 ቁጥር 18 ውስጥ እግዚአብሔር ለአብርሃም በተናገረበት ስፍራ ነው፡፡ በዚህ ምንባብ እግዚአብሔር የተስፋይቱን ምድር ድንበር የጠቀሰበትን መንገድ አድምጡ፡

*በዚያ ቀን እግዚአብሔር ለአብራም እንዲህ ብሎ ቃል ኪዳን አደረገ፡፡ "ከግብፅ ወንዝ ጀምሮ እስከ ትልቁ ወንዝ እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ ይህችን ምድር ለዘርህ ሰጥቼአለሁ፡፡" (ዘፍጥረት 15፡18)*

በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተስፋ የገባለት ምድር እስከ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ግዛት ድረስ እንደሚዘልቅ ደግሞም እስከ "ግብፅ ወንዝ" ድረስ እንደሚደርስ ይነግረዋል፡፡ በርካታ ተርጓሚዎች እንደሚናገሩት "የግብፅ ወንዝ" ዐባይን በቀጥታ የሚያመለክት ሳይሆን፣ በግብፅ ድንበር በሲና የሚገኝን አነስ ያለ ወንዝ የሚያመለክት ነው ይላሉ፡፡ በሁሉም ሁኔታ፣ ይህ ጥቅስ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እንደተገለጠው የዔድንን ድንበር የሚያመለክት ነው፡፡ የዘፍጥረት ምዕራፍ 2

ማጣቀሻ  በግልፅ እንደሚያስቀምጠው፣ እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሩ ተስፋ የሰጠው ምድር በአንድ ወቅት የዔድን ምድር ተብሎ ይጠቀስ እንደ ነበር ሙሴ ያምናል፡፡ ከሙሴ አመለካከት አንፃር፣ እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ሲጓዙ፣ ይጓዙ  የነበረው ወደ ጥንታዊው የዔድን ምድር ነበር ማለት ነው፡፡

እስራኤል ወደ ዔድን የመጓዙን አስፈላጊነት ለማስመር፣ ሙሴ የዚያን ስፍራ ቅዱስ ባህርይ ጫን ብሎ ይገልጣል፡፡ የዔድንን የተቀደሰ ስፍራነት ያመለከተው፣ እርሱ እየመራ የሚወስዳቸው የተስፋዪቱ ምድር ወደ እግዚአብሔር ልዩ ኅላዌ የመግባትን በረከት የሚቀበሉባት ምድር መሆኗን ለእስራኤል ለማስተማር ነበር፡፡

## ቅድስና

ሙሴ የዔድንን ቅድስና ለመግለጥ የተጠቀመበት ተቀዳሚ መንገድ የማደሪያውን ድንኳን ለመግለፅ ከተጠቀመበት ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ ምንም እንኳን እግዚአብሔር በሁሉ ስፍራ በአንድ ጊዜ የሚገኝ፣ በጥቅል አነጋገርም በሁሉም ስፍራ የሚኖር ቢሆንም፣ ከህዝቡ ጋር ለየት ባለ መንገድ ለመገናኘት የሚገለጥበትን የመገናኛ ድንኳን ሙሴ ሥርቷል፣ በዚህ የመገናኛ ድንኳን እግዚአብሔር ህልውናውን ይገልጣል፣ ህጉን ይሰጣል፣ የህዝቡን አምልኮ ይቀበላል በሞገሱም ይባርካቸዋል፡፡ ስለዚህ፣ ሙሴ የዔድንን ገነት የሚገልፀው የመገናኛውን ድንኳን በሚገልፅበት መልክ ነው፡፡ ይህም ዔድን እና የአሁኗ ከነዓን እግዚአብሔር በዚህ ምድር በልዩ መንገድ የሚገለጥባቸው ስፍራዎች ናቸው፡፡ በዚያ፣ እስራኤል የእግዚአብሔርን ታላቅ በረከት ትቀበላለች፡፡

ቢያንስ ሰባቱ የዔድን ገፅታዎች ልክ እንደ መገናኛው ድንኳን ሁሉ፣ የእግዚአብሔር ልዩ ህላዌ የሚገለጥበት ቅዱስ ስፍራ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ በመጀመሪያ፣ በምዕራፍ 3 ቁጥር 8 ውስጥ ሙሴ እግዚአብሔር “በገነት ውስጥ ይመላለስ ነበር” በማለት በልዩ መንገድ ይጠቅሳል፡፡ ይመላለስ ነበር ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ መግለጫ *mit halek* ((((מִתְהַלֵּךְ.)) የሚል ነው፡፡ ይህ አባባል በጣም ወሳኝ ነው ምክንያቱም ሙሴ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 ቁጥር 12 እና በሌሎችም ምንባቦች በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የእግዚአብሔርን ኅላዌ ከገለጠባቸው መንገዶች አንዱ ነበርና ነው፡፡

ሁለተኛ፣ በምዕራፍ 2 ቁጥር 9 የሕይወት ዛፍ የዔድን ገነት ማዕከላዊ ገፅታ ሆኖ መጠቀሱን እናነብባለን፡፡ ይህ የተቀደሰ ዛፍ ከእርሱ ለሚበሉ የዘላለምን ሕይወት የመለገስ ኃይል አለው፡፡ ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በግልፅ ባይናገረውም፣ በቅርብ የወጡ የከርሰ ምድር ጥናት ምርምሮች እንደሚያሳዩት በጥንታዊው ዓለም የሚገኙ በርካታ ስፍራዎች በተቀደሱ ስፍራዎች የሕይወትን ዛፍ ምስል ይዘው ተገኝተዋል፡፡ ይህ መረጃ በብርቱ የሚያመለክተን መቅረዙ፣ ማለትም ሙሴ በሠራው የመገናኛ ድንኳን የሚገኘው ባለ ሰባት ሻማ ማስቀመጫ መቅረዝ፣ የሕይወትን ዛፍ የሚገልጥ በጣም ተቀራራቢ መግለጫ ነው፡፡ በዚህ መንገድ፣ የዔድን ገነት በምድር የምትገኝ ቀደምት ቅዱስ ስፍራ መሆኗን ያሳያል፡፡

ሙሴ የዔድንን ቅድስና የገለጠበት ሦስተኛ መንገድ በአካባቢው ስለሚገኘው ወርቅና የከበረ ድንጋይ የሰጠው ትኩረት ነው፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 12 ውስጥ በዔድን አካባቢ ወርቅና የከበረ ድንጋይ በብዛት እንደሚገኝ ይገልፃል፡፡ እንደምንገምተውም፣ በዘፀአት ምዕራፍ 25  እስከ 40 በመገናኛው ድንኳን ግንባታ ወቅት ወርቅና የከበረ ድንጋይ ወሳኝ መሣሪያዎች ነበሩ፡፡

በዔድንና በመገናኘው ድንኳን መካከል የሚገኘው አራተኛው ትስስር የኪሩቤል ወይም የመላእክቱ መገኘት ነው፡፡ እንደ ምዕራፍ 3 ቁጥር 24 አገላለጥ፣ ወደ ሕይወት ዛፍ እንዳይገባ እግዚአብሔር በዔድን ገነት ውስጥ ኪሩቤልን ማስቀመጡን እናያለን፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ የመገናኛው ድንኳን የማስዋብ ሥራ በተሠራበት ነገር ሁሉ ላይ ኪሩብ አለ፡፡ ይህንንም ለምሳሌ በዘፀአት ምዕራፍ 25 ቁጥር 18 እና ምዕራፍ 37 ቁጥር 9 ውስጥ እናነባለን፡፡ እነዚህ ኪሩቦች ለእስራኤላውያን የሚያሳስቡት በሰማይ የሚገኙትን መላእክት ብቻ ሳይሆን በዔድን የሚገኘውን የተቀደሰ ስፍራ የሚጠብቁ መላእክትንም ነው፡፡

አምስተኛ፣ በምዕራፍ 3 ቁጥር 24 ውስጥ የዔድን መግቢያ "በምሥራቅ" ነው፣ ያም ማለት፣ በምሥራቅ ወገን ነው፡፡ ምናልባት ይህ ነገር በዘፀአት ምዕራፍ 27 ቁጥር 13 እና በሌሎችም በርካታ ምንባቦች የተገለጠውን ማለትም የመገናኛው ድንኳንም መግቢያ በምሥራቅ ወገን መሆኑን እስከናስተውል ድረስ ወሳኝነት የሌለው ሊመስለን ይችላል፡፡ በቅርብ መሥራቅ የሚገኙ አብዛኞቹ መቅደሶች መግቢያቸው በምሥራቅ የሆነበት ምክንያቱ ይህ ነው፡፡ ዔድን የእግዚአብሔር ቅዱስ መገኛ ሆና ተገልጣለች፡፡

ስድስተኛ፣ ሙሴ አዳም በዔድን ስለ ነበረው አገልግሎት የጠቀሰበት ቃል ሌዋውያን በመገናኛው ድንኳን ስለሚሰጡት አገልግሎት ከጠቀሰበት ቃል ጋር ተመሳሳይ ቋንቋ አለው፡፡ በምዕራፍ 2 ቁጥር 15 አዳም በዔድን የነበረውን ሃላፊነት ሙሴ እንዲህ ያስቀምጠዋል፡

> *... ያበጃትም ይጠብቃትም ዘንድ በዔድን ገነት አኖረው፡፡ (ዘፍጥረት 2፡15)*

እነዚህ አባባሎች በዘኁልቁ ምዕራፍ 3 ቁጥር 7 እና 8 ደግሞም በቁጥር 26 ውስጥ ይገኛሉ፡፡ በዚያ ስፍራ፣ ሙሴ ተመሳሳዩን መግለጫ በመጠቀም ሌዋውያን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ የሚሰጡትን አገልግሎት ገልጧል፡፡ አዳምና ሔዋን በዔድን ገነት ውስጥ እንደ ካህናት አገልግለዋል፡፡

ሰባተኛ፣ ዔድን ገነት የተበጀችው ከስድስቱ የመፍጠር ቀናት በኋላ መሆኑ ወሳኝ ነው፡፡ ቀደም ባለው ትምህርት እንዳየነው፣ ስድስቱ የመፍጠር ቀናት ወደ ላዕላይ እርከን የደረሱት በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ከቁጥር 1 እስከ 3 በተገለጠው የእግዚአብሔር የሰንበት እረፍት ነው፡፡ እጅግ በሚስብ መንገድ፣ እንደ ዘፀአት ምዕራፍ 24 ቁጥር 16 እና ቀጥሎ ባለው አገላለጥ፣ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በተራራ ላይ ለስድስት ቀናት ቆይቷል፣ በሰባተኛውም ቀን የመገናኛውን ድንኳን እንዲሠራ መመሪያ ሰጥቶታል፡፡

እነዚህ ሰባት የዔድን ገፅታዎች ሙሴ ልክ እንደመገናኛው ድንኳን ሁሉ የዔድን ገነትን እንደተቀደሰ ስፍራ ሲቆጥር ያሳዩናል፡፡ ያም ስፍራ እግዚአብሔር በዓለም ላይ የሚገለጥበት ልዩ ስፍራ ነበር፡፡ ወደዚያ ስፍራ መቅረብ ማለት ወደ እግዚአብሔር በረከቶች መቅረብ ማለት ነው፡፡

እንደተመለከትነው፣ ከነዓን ዔድን የምትገኝበት ስፍራ እንደሆነች ሙሴ ያምናል፡፡ በውጤቱም፣ በዔድን ቅዱስ ባህርይ ላይ በማትኮር፣ ሙሴ ትኩረታችንን ወደ ከነዓን ቅዱስ ባህርይ ዘወር ያደርገዋል፡፡ ወደ ከነዓን መቅረብ ማለት ገና ከጅማሬው አንስቶ እግዚአብሔር የእርሱ ማረፊያ እንዲሆን ወደ ወሰነው ስፍራ መቅረብ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ወደፊት ስለሚመጣ ቅዱስ ስፍራ ሙሴ ያስፈረውን ትምህርት መመልከት የምንችልበት የተመረጠ ምንባብ ዘዳግም ምዕራፍ 12 ቁጥር 10 እና 11 ነው፡፡ በዚያም እንዲህ ጽፏል፡

*የርዳኖስን ግን በተሻገራችሁ ጊዜ፣ አምላካችሁም እግዚአብሔር በሚያወርሳችሁ ምድር በተቀመጣችሁ ጊዜ፣ ያለ ፍርሃትም እንድትኖሩ ከከበቧችሁ ጠላቶች ሁሉ ዕረፍት በሰጣችሁ ጊዜ፣ በዚያን ጊዜ አምላካችሁ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ ወደዚያ ወደመረጠው ስፍራ፣ እኔ የማዝዛችሁ ሁሉ፣ የሚቃጠለውን መስዋዕታችሁን፣ ሌላ መስዋዕታችሁንም፣ ዐሥራታችሁንም፣ በእጃችሁ ያነሣችሁትንም ቁርባን፣ ለእግዚአብሔርም ተስላችሁ የመረጣችሁትን ስእለታችሁን ሁሉ ውሰዱ፡፡ (ዘዳግም 12፡10-11)*

ይህ ምንባብ ሙሴ ስለ ከነዓን ምድር ካለው ማዕከላዊ ራእይ አንዱን ገፅታ ያሳያል፡፡ አንድ ቀን ከነዓን የእግዚአብሔር ኅላዌ ቋሚ ስፍራ፣ የያህዌ መቅደስ እንደምትሆን አፅንዖት ሰጥቶበታል፡፡

እርግጠኛ ለመሆን፣ በሙሴ ዘመን የነበረችው ከነዓን ቀደም ብሎ የነበረችው ዔድን ጥላ ነበረች፡፡ ሰሎሞን በኢየሩሳሌም መቅደሱን ሲገነባ እንኳን፣ የተስፋዪቱ ምድር ከኃጢአት ፈጽሞ አልተዋጀችም ወይም ወደ ቀደመው ፍፅምናዋ አልተመለሰችም ነበር፡፡ ሆኖም፣ ሙሴ ስለ ዔድን ቅድስና ሲጽፍ፣ አንድ ቀን ምድራቸው ምን መምሰል እንዳለባት የነበረውን ራዕይ ለእስራኤላውያን ይገልጥላቸዋል፡፡ ወደ ተስፋዪቱ ምድር መድረስ ማለት ወደ ዔድን መቅረብ፣ ማለትም እግዚአብሔር በምድር ወደሚገለጥበት ቅዱስ መገኛ መቅረብ ማለት ነው፡፡ ልክ እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምንና ሔዋንን በዔድን እንዳስቀመጣቸው ሁሉ፣ አሁን ደግሞ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ከነዓን ያመጣቸዋል፣ እነርሱም አንድ ጊዜ በዚያ ስፍራ ከተቀመጡ፣ አገሪቱ በጠቅላላ በእግዚአብሔር ኅልውና ውስጥ የመኖርን በረከት ታጣጥማለች፡፡

አዳምና ሔዋን በዔድን ያገኙትን በረከት እስራኤልን በተስፋዪቱ ምድር ለሚጠብቃት ፀጋ ተምሳሊት አድርጎ ሙሴ መግለጡን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በምዕራፍ 2 እና 3 የሚገኘውን ሁለተኛ ርዕስ ወደ መመልከቱ እንሸጋገር፡፡ ያም የአዳምና የሔዋን ታማኝነት በእግዚአብሔር መፈተኑ ነው፡፡ ይህም ጭብጥ በሙሴ አቀራረብ ውስጥ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡

## ታማኝነት

የታማኝነት መሪ ሃሳብ ሙሴ ስለ ዔድን ለፃፈው ታሪክ ወሳኝ ነው፡፡ ምንም እንኳ ዔድን የአስደናቂ በረከት ስፍራ ብትሆንም፣ ሞራላዊ ሃላፊነት አብሮ ያለባት ስፍራም ናት፡፡ ሙሴ ለዚህ እውነታ አፅንዖት የሰጠበት ምክንያት እስራኤል እየሄዱበት ያለው ስፍራ ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት ታማኝ መሆንን የሚጠይቅ መሆኑን ለማስታወስ ነው፡፡

ሙሴ በዚህ መሪ ሃሳብ ላይ ለምን አፅንዖት እንደሰጠ ለመገንዘብ፣ ሁለት ጉዳዮችን መመርመር ያስፈልገናል፡፡ እነርሱም፣ በዔድን ገነት ተዓማኒነት መመዘኛ መሆኑ እና በከነዓንም ተዓማኒነት መመዘኛ መሆኑ ናቸው፡፡ አስቀድመንም በዔድን ገነት እግዚአብሔር ይጠብቅ ስለነበረው ታማኝነት እንመልከት፡፡

### በዔድን

በዔድን ውስጥ የታማኝነት ጭብጥ የተገለጠው ገና በምዕራፍ 2 ጅማሬ ላይ ሲሆን በምዕራፍ 2 እና 3 በጠቅላላም ደጋግሞ ተገልጧል፡፡ በበርካታ መንገዶችም፣ የእነዚያ ምዕራፎች ማዕከላዊ

ሃሳብም ነው፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 16 እና 17 እግዚአብሔር የአዳምን እምነት የፈተነበትን መንገድ አድምጡ፡

*እግዚአብሔር አምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው፡፡ ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካምና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና፡፡ (ዘፍጥረት 2፡ 16-17)*

እግዚአብሔር የመጀመሪያ ወላጆቻችንን ለምን ከዚያ ዛፍ እንዳይበሉ እንደከለከላቸው ግልፅ አይደለም፤ መልካሙንና ክፉውን ማወቅ በሌሎቹ የቅዱሳት መጻሕፍት ክፍሎች ተመስግኖ እናያለን፡፡ ይህ ጥርጣሬ እንዳለ ሆኖ፣ አዳምና ሔዋን ለእርሱ ታማኝ መሆን አለመሆናቸውን እግዚአብሔር እየፈተሸ መሆኑ ግን በጣም ግልፅ ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ቢታዘዙ ኖሮ፣ ከእግዚአብሔር እጅግ የላቀ በረከትን ይቀበሉ ነበር፡፡ እምቢተኛ ከሆኑ ግን፣ የእግዚአብሔር ፍርድ ይወድቅባቸዋል፡፡ ዔድን የተቀደሰች ስፍራ ናት፣ እናም በዚያ የሚኖሩ ሰዎችም የቀደሱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

## በከነዓን

በዔድን ገነት ታማኝነት የተፈተነ በመሆኑ ላይ በማትኮር፣ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እየመራቸው ካሉት እስራኤላውያንም ተመሳሳይ ታማኝነት የሚጠበቅባቸው መሆኑን በአፅንዖት ያሳስባል፡፡ ሙሴ እስራኤልን ወደ ተስፋዪቱ ምድር ሲመራ፣ እግዚአብሔር ታማኝ እንዲሆኑለት የሚፈልግ መሆኑን ደጋግሞ አስጠንቅቋቸዋል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ያነሳውን ትምህርት በዘዳግም ስምንተኛ ምዕራፍ ውስጥ ቅልብጭ ባለ አነጋገር ጠቅለል አድርጎ አቅርቧል፡፡ በዘዳግም ምዕራፍ 8 ቁጥር 1 እንዲህ እናነብባለን፡-

*በሕይወት እንድትኖሩ፣ እንድትበዙም፣ እግዚአብሔርም ለአባቶቻችሁ ወደ ማለላቸው ምድር ገብታችሁ እንድትወርሱአት፣ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን ትእዛዝ ሁሉ ታደርጉ ዘንድ ጠብቁ፡፡ (ዘዳግም 8፡1)*

እስራኤል ወደ ከነዓን ምድር ለመግባትና ለመውረስ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን እንደሚጠበቅባቸው ይህ ምንባብ በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ እንዲያውም፣ ህዝቡ በምድረበዳ ሲንከራተት፣ እንዴት መቀደስ እንዳለባቸው እግዚአብሔር እስራኤልን እየፈተነ ነበር፡፡ በዘዳግም ምዕራፍ 8 ቁጥር 2 እንዲህ እናነብባለን፡፡

*አምላክህ እግዚአብሔር ይፈትንህ ዘንድ፣ በልብህም ያለውን ትዕዛዙን ትጠብቅ ወይም አትጠብቅ እንደሆነ ያውቅ ዘንድ፣ ሊያስጨንቅህ በእነዚህ በአርባ ዓመታት በምድረ በዳ የመራህን መንገድ ሁሉ አስብ፡፡ (ዘዳግም 8፡2)*

ከዚህም ባሻገር፣ አንድ ጊዜ እስራኤል ወደ ቅድስቲቱ ምድር ከገቡ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆኖ መዝለቅ አለበለዚያ ግን ሊያገኙ የሚገባቸውን ጥቅም ማጣት እንደሚጠብቃቸው ሙሴ ግልፅ አድርጎላቸዋል፡፡ እስኪ በዘዳግም ምዕራፍ 8 ከቁጥር 10 እስከ 20 ይህንን እንዴት እንዳሰፈረው አዳምጡ፡

*ዛሬ አንተን የማዝዘውን ትእዛዙንና ፍርዱን ሥርዓቱንም ባለመጠበቅ አምላክህን እግዚአብሔርን እንዳትረሳ ተጠንቀቅ፤ .... አምላክህንም እግዚአብሔርን ብትረሳ፣ ሌሎችንም አማልክት ብትከተል ብታመልካቸውም ብትሰግድላቸውም፣ ፈጽሞ እንድትጠፉ እኔ ዛሬውኑ እመሰክርባችኋለሁ፡፡ የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ቃል ስላልሰማችሁ እግዚአብሔር ከፊታችሁ እንደሚያጠፋቸው እንደ አሕዛብ እንዲሁ እናንተ ትጠፋላችሁ፡፡ (ዘዳግም 8፡10-20)*

ልክ እንደ አዳምና ሔዋን ሁሉ፣ እስራኤልም በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ላይ ወደማመፅ ሊያዘነብሉ እንደሚችሉ ሙሴ ያውቃል፡፡ በእነዚህም ዝንባሌዎች ምክንያት፣ ሙሴ በዔድን ገነት አዳምና ሔዋን በተፈተኑት ፈተና ላይ በማትኮር በከነዓን ምድር ለመኖር የሚፈልግ ሁሉ ታማኝ መሆንን እግዚአብሔር  እንደሚጠብቅበት ያስጠነቅቃል፡፡ እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር ከእስራኤል ፍፅምናን አይጠብቅም ደግሞም ማንም ሰው ታማኝ መሆን የሚችለው በእግዚአብሔር ጸጋ ብቻ ነው፡፡ ሆኖም፣ እስራኤል ልክ አዳምና ሔዋን በዔድን እንዳደረጉት ሁሉ የእግዚአብሔርን ህግጋት በጉልህ በመተላለፍ ከእርሱ ዘወር ካሉ፣ የተስፋይቱን ምድር በረከት ሊቋደሱ አይችሉም፡፡ እስራኤላውያን ወደ ተስፋይቱ ምድር እንዲገሰግሱ ሙሴ ሲያበረታታቸው፣ በምድሪቱ የሚኖርበትን የሕይወት ገፅታ እንዲያስታውሱ ሙሴ ያሳስባል፡፡

የዘዳግም ምዕራፍ 8 አስተምህሮ በልቡናችን ይዘን፣ ሙሴ ከአዳምና ከሔዋን ይጠበቅባቸው በነበረው ታማኝነት ላይ ያተኮረበትን ዋና ምክንያት እንመለከታለን፡፡ እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት ታማኝ ሆኖ በመዝለቅ አዳምና ሔዋን ያደረጉትን እንዲቀለብሱ ለማበረታታት ይህንን ጉዳይ አፅንዖት ሰጥቶበታል፡፡ አዳምና ሔዋን በገነት ውስጥ ተፈተኑ በደልንም በመሥራታቸው ከዚያ ተባረሩ፡፡ በሙሴ ዘመን፣ እስራኤል ገና ከዔድን ገነት ውጪ ነበረች፡፡ ሆኖም እግዚአብሔር እስራኤል እንደገና ወደ ዔድን እንድትገባና በእግዚአብሔር በረከት ውስጥ እንድትኖር ለማዘጋጀት ይፈትናቸው ነበር፡፡

ሙሴ በዔድን ገነት ስለነበረው ፈተና ሲፅፍ፣ በድሮ ዘመን በአዳምና በሔዋን የጥንት ታሪክ ምን እንደተከናወነ ለእስራኤላውያን ሊያብራራላቸው ብቻ እንዳልጻፈ ተመልክተናል፡፡ በእርሱ በራሱም ዘመን ምን እየተከናወነ እንዳለም አብራርቷል፡፡ እስራኤላውያንም በዔድን ገነት የመኖርን አስደናቂ የበረከት ሕይወት እግዚአብሔር አቅርቦላቸው ነበር፡፡ ሆኖም፣ ልክ እንደ አዳምና ሔዋን ሁሉ፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ መሆን ካቃታቸው እነዚህን በረከቶች ሊቋደሱ አይችሉም፡፡ እንደ ቅዱስ ህዝብ እንዲኖሩና ለእግዚአብሔር ህግጋትም ሙሉ በሙሉ እንዲገዙ ሙሴ ለእስራኤላውያን ጥሪ ያቀርባል፡፡ ወደ ምድሪቱ መግባትና በዚያም በሰላም መኖር የሚችሉት በዚያን ጊዜ ብቻ ነው፡፡

እስከ አሁን ድረስ ሙሴ የዔድንን ምድርና የከነዓንን ምድር የእግዚአብሔር የበረከት ስፍራዎች አድርጎ መግለጡን ተመልክተናል፣ በተጨማሪም ሁለቱም ምድሮች በውስጣቸው ከሚኖሩ ሰዎች ታማኝ አገልጋይ መሆንን እንደሚጠይቁ እንዴት አድርጎ እንዳመለከተም አይተናል፡፡ አሁን ደግሞ የዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 ቀደምት ትርጉም ለእስራኤል ያለውን ፋይዳ የሚያሳየውን ሦስተኛ እርከን እናያለን፡፡ ያም የአዳምና የሔዋን አለመታዘዝ ያመጣው መዘዝ ነው፡፡

# መዘዞች

በገነት ውስጥ አለመታዘዝ ያመጣውን መዘዝ ለመመልከት፣ የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ሦስት ውጤቶችን እንመለከታለን፡፡ እነርሱም፡ ሞት፣ ህማምና መባረር ናቸው፡፡

## ሞት

በመጀመሪያ ደረጃ፣ በኃጢአት ጦስ ምክንያት እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን በሞት እንደቀጣቸው ሙሴ ያብራራል፡፡ ይህ ጭብጥ በመጀመሪያ ተገልጦ የምናገኘው በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 እግዚአብሔር ለአዳም በሰጠው ማስጠንቀቂያ ውስጥ ነው፡፡ በዚያ፣ እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል፡-

> *ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና፡፡ (ዘፍጥረት 2፡17)*

“ሞትን ትሞታለህና” የሚሉት ቃላት ሞት አይቀሬ መሆኑን የሚያመለክት ሐረግ ይመሠርታሉ፡፡ ይህ ሰዋሰዋዊ አወቃቀር የሙሴ ህግ ከሚያስከትለው ቅጣት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ አደገኛ ወንጀል በሚፈፅሙ ላይ የሙሴ ህግ ቅጣት ሲበይን፣ “በእርግጥ ትሞታለህ” ወይም “በእርግጥ ይሞታሉ” የሚለውን ሙሴ ያውጃል፡፡ የዚህ ምንባብ ህጋዊ አውድ በብርቱ እንደሚነግረን እነዚህ መግለጫዎች የሞት ፍርድ የሚተላለፍበትን ቀመር ያመለክታሉ፡፡ እግዚብሔር አዳምና ሔዋን ወዲያውኑ ይሞታሉ አላለም፣ ሆኖም ሞት ኃጢአትን ተከትሎ መምጣቱ እንደማይቀር የተረጋገጠ ነው፡፡

በዚህ መሠረት በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 ቁጥር 17 እግዚአብሔር ያስተላለፈው ብይን አዳም በሞት ፍርድ ውስጥ የወደቀ መሆኑን እንድንረዳ ያደርገናል፡፡ የሞት እርግማን ወደቀበት፡፡ እነዚህ የአዳም ኃጢአት መዘዞች ሞት ወደ ዓለም እንዴት እንደገባ የሚያብራሩ መሆኑን ሙሴ በእርግጠኝነት ጽፏል፣ ዓላማው ግን እርሱ ከሚጽፍላቸው እስራኤላውያን ልምምድ ጋር በቀጥታ ይገናኛል፡፡ ከሞት ጋር በደንብ ይተዋወቃሉ፡፡ የሙሴ ተደራሲያን ከግብፅ ከወጡ የመጀመሪያ ትውልዶች መካከል አብዛኞቹ በእግዚአብሔር ላይ በማመጻቸው ምክንያት በምድረ በዳ ሲሞቱ ተመልክተዋል፡፡ ሙሴ በዘኊልቁ ምዕራፍ 26 ቁጥር 65 እንደጻፈው፡-

> *እግዚአብሔር ስለ እነርሱ በእውነት በምድረ በዳ ይሞታሉ ብሎ ተናግሯልና፣ ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብ ከነዌም ልጅ ከኢያሱ በቀር ከእነርሱ አንድ ሰው ስንኳ አልቀረም፡፡ (ዘፍጥረት 26፡65)*

“በእውነት ይሞታሉ” የሚለውንና ሙሴ በኤድን ገነት ለአዳምና ለሔዋን የተጠቀመውን ቋንቋ እዚህም በድጋሚ እንመለከተዋለን፡፡

በዚህ ረገድ፣ የአዳምንና የሔዋንን ታሪክ የሚያደምጡ እስራኤላውያን፣ በምድረ በዳ የመሞታቸውን ታሪክ አዳምና ሔዋን በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ላይ በማመፅ ከገጠማቸው ሞት ጋር ያገናኙታል፡፡ በዔድን ገነት በእግዚአብሔር ትዕዛዛት ላይ የተፈፀመ አመፅ ያስከተለው መዘዝ በሰው

ዘር የመጀመሪያ ወላጆች ላይ ሞት  አስከተለ፣ ደግሞም በሙሴ ዘመን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት አሳዛኝ በሆነ መንገድ መታዘዝ ባቃታቸው እስራኤላውያንም ያው ፍርድ ጸና፡፡

## ህማም/ስቃይ

የዘፍጥረትን ዘገባ በምናነብበት ወቅት፣ ሞት በአዳምና በሔዋን ላይ ወዲያውኑ እንዳልመጣ በግልፅ ተቀምጧል፡፡ እግዚአብሔር በመጀመሪያ አዳምና ሔዋን በህማም ውስጥ እንዲኖሩ ፈቀደ፡፡ በአንድ በኩል፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 16 ውስጥ እንዲህ እናነብባለን፡፡

*ለሴቲቱም አለ፣ "በፀነስሽ ጊዜ ጭንቅሽን እጅግ አበዛለሁ፡፡ በጭንቅ ትወልጃለሽ፤ ፈቃድሽም ወደ ባልሽ ይሆናል፣ እርሱም ገዥሽ ይሆናል፡፡" (ዘፍጥረት 3፡16)*

በሌላ በኩል ደግሞ፣ አዳም ስቃይ በሞላበት ኑሮ እንዲኖር እግዚአብሔር ረገመው፡፡ በዘፍጥረት 3፡17 እንዲህ እናነብባለን፡

ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን፤ በሕይወት ዘመንህም ሁሉ በድካም ከእርስዋ ትበላለህ፡፡   (ዘፍ 3፡17)

በገነት ውስጥ በኃጢአት ምክንያት ስለመጣው መዘዝ ሙሴ ከተናገራቸው ነገሮች ሁሉ፣ ይህ መንታ የሰው ዘር ህማም ትኩረት ዘገባውን ለእስራኤል ከመጻፉ ዓላማ ጋር በእጅጉ የሚጣጣም ነው፡፡ ከከነዓን ምድር ውጪ በቆዩባቸው ጊዜያት ሁሉ በዚህ ስፍራ የተጠቀሱት ስቃዮች በጠቅላላ ደርሰውባቸዋል፡፡ ግን ሙሴ ሕይወትን በተስፋይቱ ምድር የገለጠበትን መንገድ አድምጡ፡፡ በዘዳግም ምዕራፍ 11 ከቁጥር 10 እስከ 12 እንዲህ እናነብባለን፡፡

*ትወርሳት ዘንድ የምትገባባት ምድር፣ በአትክልት ስፍራ እንደሚዘሩ ዘርህን እንደዘራህባት፣ በእግርህም እንዳጠጣሃት፣ እንደ ወጣህባት እንደ ግብፅ ምድር አይደለችም፡፡ ነገር ግን ትወርሱአት ዘንድ ተሻግራችሁ የምትገቡባት ምድር ኮረብታና ሸለቆ ያለባት አገር ናት፤ በሰማይ ዝናብ ውኃ ትረካለች፡፡ አምላክህ እግዚአብሔር የሚኀበኛት አገር ናት፤ ከዓመቱ መጀመሪያ እስከ ዓመቱ መጨረሻ ድረስ የአምላክህ የእግዚአብሔር ዓይን ሁል ጊዜ በእርስዋ ላይ ነው፡፡ (ዘዳግም 11፡10-12)*

በአጭሩ፣ ሙሴ እስራኤልን እየወሰደ ያለባት ምድር ከከነዓን ምድር ውጪ የገጠማቸው ስቃይ ሁሉ የሚወገድባት ምድር ናት፡፡ አያይዞም፣ ሙሴ በአዳምና በሔዋን ላይ ስለመጣው ስቃይ ሲጽፍ፣ እስራኤላውያን ተደራሲያኑ ስቃይ ከሚያስከትልባቸው፣ ካለመታመን ራሳቸውን እንዲያነፁ እና ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ ያን ካደረጉም ወደ ከነዓን እንደሚመለሱና በእግዚአብሔር የበረከት ስፍራ ውስጥ የሚገኘውን የደስታ ሕይወት እንደሚለማመዱ እየነገራቸው ነው፡፡

## መባረር

ሦስተኛው የአዳምና የሔዋን ያለመታዘዝ መዘዝ የሚገኘው በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 22 ውስጥ ነው፡፡ በዚያ የሰፈሩትን ቃላት ልብ በሏቸው፡፡

*እግዚአብሔር አምላክም አለ፡፡ እነሆ አዳም መልካምንና ክፉን ለማወቅ ከእኛ እንደ አንዱ ሆነ፤ አሁንም እጁን እንዳይዘረጋ፣ ደግሞም ከሕይወት ዛፍ ወስዶ እንዳይበላ፣ ለዘላለምም ሕያው ሆኖ እንዳይኖር፤ (ዘፍጥረት 3፡22)*

ይህ ምንባብ የሕይወት ዛፍ የሰው ዘር "ለዘላለም እንዲኖር" የምታስችለው እንደነበረች ግልፅ ያደርጋል፡፡ ለስቃይና ለሞትም የመጨረሻው መልስ ነበር፡፡ አዳምና ሔዋን በዚያን ወቅት እንዲበሉ ግን እግዚአብሔር አልፈቀደም፡፡ ከገነትና በውስጥዋ ካለው የሕይወት ዛፍ ተባረሩ፡፡

የሰው ዘር ወደ ሕይወት ዛፍ የመቅረቡ ዕድል ግን ለዘላለም አልተዘጋበትም፡፡ የተቀሩት ቅዱሳት መጻሕፍት በግልፅ እንደሚያስቀምጡት፣ ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው የሚዘልቁት ግን በስተመጨረሻው ከዚያ ዛፍ ይበላሉ፡፡ በራእይ ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 ሐዋርያው ዮሐንስ ስለ ሕይወት ዛፍ የተናገረውን አድምጡ፡

*… ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ፡፡ (ራእይ 2፡7)*

ዮሐንስ እየተናገረ ያለው ክርስቶስ ወደ ምድር ሲመለስ ስለሚሆነው የመጨረሻ ዘመን ነው፡፡ ቃላቶቹ ግን፣ ስለዚህ የሕይወት ዛፍ ሙሴ ለምን እንደጻፈ ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ሲበድሉ፣ ወደ ሕይወት ዛፍ የሚወስደውን መንገድ እግዚአብሔር ዘጋው፣ በሙሴ ዘመን ግን፣ ለእስራኤል እንደገና መንገዱን ከፈተው፣ በዚያም ወደ ከነዓን ምድር ሲመለሱ ቢያንስ የሕይወትን በረከት ቅምሻውን እንዲያጣጥሙ አድርጓል፡፡ በዘዳግም ምዕራፍ 30 ቁጥር 19 እና 20 ሙሴ ያስቀመጠበትን መንገድ አድምጡ፡

*በፊታችሁ ሕይወትንና ሞትን በረከትንና መርገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰክራለሁ፤ አንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤ እግዚአብሔርም ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያዕቆብም እንዲሰጣቸው በማለላቸው በምድሪቱ ትቀመጥ ዘንድ፣ እርሱ ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ፡፡ (ዘዳግም 30፡19-20)*

እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር ታማኝ ከሆኑ በከነዓን ምድር ረጅም ዕድሜንና ደስታን የማግኘት ዕድል አላቸው፡፡

ልክ አዳምና ሔዋን ወደ ሕይወት ዛፍ የመግባት ዕድል እንደተነፈጉ ሁሉ፣ በሙሴም ዘመን እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጠው በዚያ ከሚገኘው የበረከት ሕይወት የገሚሱን ቅምሻ ብቻ ነው፡፡ ይህ የሕይወት ልምምድ ክርስቶስ ሲመጣ እንደምንቀበለው የዘላለም ሕይወት የተሟላ አይደለም፡፡ በክርስቶስ ሊመጣ ያለው በረከት ገሚስ ቅምሻ ብቻ ነው፡፡ በተስፋዪቱ ምድር የረጅም ዕድሜ በረከትን ሊያጣጥሙ የሚችሉበትን ዕድል በሙሴ አማካይነት ሰጥቷቸው ነበር፡፡

በዔድን ገነት አዳምና ሔዋን የፈፀሙት በደል በዓለም ላይ የኃጢአት ምንጭ የመሆኑ ዘገባ ብቻ ከመሆን እጅግ የዘለለ መሆኑን ተመልክተናል፡፡ በዔድን እና በከነዓን መካከል ትስስሮችን በመፍጠር፣ ሙሴ እስራኤላውያን አንባቢዎቹን ስለ ራሳቸው ሕይወት አስተምሯቸዋል፡፡ በዚያም የተስፋይቱ ምድር ለእነርሱ እንዴት አስደናቂ እንደምትሆን ያውቁ ነበር፡፡

የዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 ስነ-ጽሑፋዊ አወቃቀርና ቀደምት ትርጉም ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ ሦስተኛውን ጥያቄ ለመጠየቅ እንዘጋጃለን፡፡ ይህንን ምንባብ ዛሬ እናዛምደው ዘንድ አዲስ ኪዳን የሚያስተምረን እንዴት ነው?

## 4. ዘመነኛው ተዛምዶ

ሙሴ ይህንን ምንባብ የጻፈው እስራኤላውያን አንባቢዎቹ ከአዳምና ከሔዋን ስህተት በመራቅ ወደ ከነዓን በመግባት ወደ ገነት ለመመለስ እንዲጓዙ ለማበረታታት መሆኑ ግልጽ ሆኖልናል፡፡ ግን እነዚህ ለእስራኤል የተሰጡ መመሪያዎች ከእኛ ጋር ምን ጉዳይ አላቸው? በቀላሉ ብናስቀምጥ፣ ሙሴ በገነት ውስጥ የተከናወነውን የኃጢአት ታሪክ በማንሳት እስራኤላውያን የአዳምን እርምጃዎች በመመርመርና በመቀልበስ እንደገና ወደ ገነት በመመለስ የመኖርን ድነት እንዲያገኙ እንዳበረታታ ሁሉ፣ የአዲስ ኪዳን ጸሐፍትም በክርስቶስ የሚገኘው ድነት ወደ ገነት መመለስ መሆኑን አስተምረዋል፡፡

የዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 አዲስ ኪዳናዊ አጠቃቀም ከክርስቶስ ጋር በተገናኘ መንገድ እንመረምራለን፡፡ ይህንንም የምናደርገው አዘውትረን በምንጠቀምበት መንገድ በክርስቶስ መንግሥት ሦስት እርከኖች ላይ በማትኮር ነው፡፡ ይህ ምንባብ በክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት በመንግሥቱ ምሥረታ ላይ እንዴት እንደሚተገበር በመመልከት እንጀምርና በመቀጠል ደግሞ ዛሬ በእግዚአብሔር መንግሥት ዕድገት ውስጥ ለእኛ ምን እንደሚናገር እናያለን፡፡ በመጨረሻ፣ በክርስቶስ ዳግም መምጣት ስለሚከናወነው የክርስቶስ መንግሥት ፍፃሜ ይህ ምንባብ ምን እንደሚስተምር አዲስ ኪዳን የሚያቀርበውን ሃሳብ እንመለከታለን፡፡ አስቀድመን የመንግሥቱን ምሥረታ እንመልከት፡፡

### ምሥረታ

ክርስቶስ ለዓለም ስለሚያመጣው ድነት አዲስ ኪዳን ከሚናገርባቸው ነገሮች አንዱ በምድራዊ አገልግሎቱ ስለሆነው ነገር መተረክ ነው፡፡ በመንግሥቱ ምሥረታ ወቅት ክርስቶስ አዳምና ሔዋን በዔድን የሠሩትን ቀልብሶታል፡፡ በምድራዊ አገልግሎቱ ወቅት አዳምና ሔዋን የሳቱትን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ክርስቶስ ፈጽሟል፡፡ በመጀመሪያ፣ ይህንን የአዲስ ኪዳን አስተምህሮ ገጽታ የምንመረምረው ይህ መሪ ሃሳብ በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ እንዴት እንደተገለጠ እና ሁለተኛ፣ በማቴዎስ ወንጌል ውስጥ እንዴት እንደተገለጠ በመመልከት ነው፡፡ እስኪ በጳውሎስ አመለካከት እንጀምር፡፡

#### ጳውሎስ

ጳውሎስ አመለካከቱን በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 14 ውስጥ ቅልብጭ ባለ አነጋገር አጠቃልሎ አቅርቦታል፡፡ በዚያም እንዲህ ጽፏል፦

> *ይሁን እንጂ ከአዳም ጀምሮ እስከ ሙሴ ድረስ ባሉት፣ እንደ አዳም ሕግን በመጣስ ኀጢአት ባልሠሩት ላይ እንኳ ሞት ነገሠ፤ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳሉ ነበረ፡፡ (ሮሜ 5፡14)*

ጳውሎስ አዳም ይመጣ ዘንድ ላለው አምሳል ነው ማለቱን ልብ በሉ፡፡ የተቀረው የሮሜ ምእራፍ 5 ክፍል “ሊመጣ ያለው” ክርስቶስ መሆኑን ግልፅ አድርጎታል፡፡ ጳውሎስ በሮሜ ምዕራፍ 5 ቁጥር 18 እና 19 ውስጥ ጉዳዩን ጠቅለል ያደረገበትን መንገድ አድምጡ፡

> *ከእንግዲህ በአንድ ሰው መተላለፍ የተነሣ ኩነኔ በሁሉ ሰው ላይ እንደ መጣ፣ እንዲሁም በአንዱ የጽድቅ ሥራ ለሰው ሁሉ ሕይወትን የሚሰጥ ጽድቅ ተገኘ፡፡ በአንዱ ሰው አለመታዘዝ ብዙዎች ኀጢአተኞች እንደ ሆኑ፣ በአንዱ ሰው መታዘዝ ደግሞ ብዙዎች ጻድቃን ይሆናሉ፡፡ (ሮሜ 5፡18-19)*

በዚህ ስፍራ ጳውሎ እንዴት እንዳስቀመጠው አስተውሉ፡፡ የአዳም አንድ ጊዜ መተላለፍ ለህዝብ ሁሉ እርግማንን አስከተለ፣ የክርስቶስ አንድ የጽድቅ ሥራ ግን ለሰው ሁሉ  ጽድቅን አስገኘ፡፡ ለምን እንዲህ ሆነ? በአንድ ሰው፣ በአዳም አለመታዘዝ ምክንያት ሁላችን በደለኞች ሆንን፡፡ የአንዱ፣ የክርስቶስ መታዘዝ ግን ጻድቃን አደረገን፡፡

ይህ አስተምህሮ ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች የተለመደ ነው፡፡ ሙሴ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 እንዳስተማረ፣ አዳም አንድ ሰው ነበር፣ የእርሱ ተግባር ግን የእርሱ ወገን በሆኑ ሁሉ መዘዝ አስከተለባቸው፡፡ የአዳም ኀጢአት በሰው ዘር ሁሉ ላይ ሞትን አስከተለ ምክንያቱም እርሱ በእግዚአብሔር ፊት የእኛ ወኪል ነበርና፡፡ በአዳም የኃጢአት ውጤት ምክንያት፣ እኛ ሁላቸን ከእግዚአብሔር የበረከት ገነት ውጭ ተወለድን በሞትም እርግማን ስር ወደቅን፡፡ ሆኖም እንደዚያው ሁሉ፣ አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረን፣ ክርስቶስ በእርሱ ያመኑ ሁሉ የቃል ኪዳን ምትካችን ሆነ፡፡ ከአዳም አለመታዘዝ በተቃራኒው፣ የክርስቶስ ለእግዚአብሔር መታዘዝ በእርሱ ለተቆጠሩት ሁሉ ጽድቅንና ሕይወትን አስገኘላቸው፡፡

ከዚህ አስተምህሮ የአዳምን የኀጢአት ታሪክ በሕይወታችን ከማዛመድ አንፃር በጣም ወሳኝ የሆነን ትምህርት እናገኛለን፡፡ የጠፋው ገነት ተመልሶ ሊገኝ የሚችልበት ብቸኛ መንገድ በክርስቶስ የጽድቅ መታዘዝ ብቻ ነው፡፡ በራሳችን የጽድቅ ሥራዎች ወደ ገነት ልንገባና በእግዚአብሔር ፊት ልንቆም አንችልም፡፡ ከእኛ ቀድሞ ወደ ገነት የሚገባ ፍፁም ምትክ ያስፈልገናል፣ ያም ምትክ ክርስቶስ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ኅላዌ ውስጥ የዘላለምን ሕይወት ድነት ልናገኝ የምንችለው ክርስቶስ ለአብ ፍፁም በመታዘዙ ምክንያት ብቻ ነው፡፡ በምድር አገልግሎቱ ወቅት፣ ኢየሱስ ወደ ገነት መግባት የሚቻልበትን መብት አስገኘ፣ እናም በእርሱ የሚያምኑ ብቻ ከእርሱ ጋር ወደ ገነት ይገባሉ፡፡

ጳውሎስ በአዳምና በክርስቶስ መካከል ስላለው ግንኙነት መናገሩ በሌሎች የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ይደገፋል፡፡ ይህ መሪ ሃሳብ በማቴዎስ ወንጌል እንዴት እንደተገለጠ እንመልከት፡፡

## ማቴዎስ

ክርስቶስ የአዳምን ኃጢአት የቀለበሰበትን መንገድ በምዕራፍ 4 ከቁጥር 1 እስከ 11 (ተጓዳኝ ምንባቡን በሉቃስ ምእራፍ 4 ከቁጥር 1 እስከ 13 ታገኛላችሁ) ውስጥ ስለ ክርስቶስ መከራ በመዘገብ ማቴዎስ ልዩ ትኩረት አድርጓል፡፡

በበርካታ የተለያዩ መንገዶች፣ የክርስቶስ መከራ ታሪክ አዳምና ሔዋን በዔድን ከነበራቸው ልምምድና ሙሴም ስለ አዳምና ሔዋን በመጻፍ እስራኤላውያንን ከሞገተበት ታሪክ ጋር ተዛማጅነት አለው፡፡ በመጀመሪያ፣ ኢየሱስ መከራን የተቀበለበት ስፍራ፣ ሙሴን ይከተሉ ከነበሩ እስራኤላውያን ታሪክ ጋር ይያያዛል፡፡ እንደ ማቴዎስ ምዕራፍ 4፡1 አገላለጥ፣ ልክ እግዚአብሔር እስራኤልን ወደ ምድረበዳ እንደ መራ ሁሉ፣ ኢየሱስም በመንፈስ ወደ ምድረ በዳ ተመርቷል፡፡

እስራኤል መታዘዝና አለመታዘዟን እግዚአብሔር በምድረ በዳ እንደፈተነ ሁሉ፣ ክርስቶስም በምድረ በዳ ተፈትኗል፡፡

ሁለተኛ፣ ኢየሱስ በምድረ በዳ የቆየባቸው ቀናት ከእስራኤል ልምምድ ጋር ተጓዳኝ ነው፡፡ እስራኤል በምድረ በዳ ለአርባ ዓመታት እንደቆየች ሁሉ፣ ማቴዎስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 2 እንደሚያሳየን ኢየሱስም በምድረ በዳ ለአርባ ቀናት ቆይቷል፡፡

ሦስተኛ፣ በክርስቶስ መፈተን ውስጥ መራብ ወሳኝ ገፅታ ነው፡፡ በማቴዎስ 4 ቁጥር 3 ውስጥ ኢየሱስ ድንጋዩን ወደ ዳቦ እንዲለውጥ ሰይጣን ፈትኖታል፡፡ ይህ የክርስቶስ መፈተን እስራኤልም በምድረ በዳ ስለ ውሃና ስለ ምግብ ከመፈተኗ ጋር ይጓደናል፡፡

አራተኛ፣ ኢየሱስ ራሱም እያለፈበት ያለው ነገር ከእስራኤል መፈተን ጋር ያለውን ቁርኝት ከቅዱሳት መጻሕፍት በመጥቀስ አያይዞታል፡፡ በማቴዎስ ምዕራፍ 4 ቁጥር 4 ውስጥ ኢየሱስ ዘዳግም ምዕራፍ 8 ቁጥር 3 ጠቅሷል፡፡ በማቴዎስ 4 ቁጥር 7 ደግሞ ዘዳግም ምዕራፍ 6 ቁጥር 16 ጠቅሷል፤ በማቴዎስ 4 ቁጥር 10 ዘዳግም ምዕራፍ 6 ቁጥር 13 ጠቅሷል፡፡ ከዘዳግም የተወሰዱት ምንባቦች ሙሴ የእስራኤልን በምድረበዳ መፈተን የገለጠባቸው ናቸው፡፡ ኢየሱስ እነዚህን ምንባቦች በመጥቀስ፣ የእርሱን መፈተን ከእስራኤል መፈተን ጋር በቀጥታ አገናኝቶታል፡፡

ማቴዎስ ስለኢየሱስ መፈተን ያቀረበው ዘገባ በዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 ሙሴ አስቀድሞ ለእስራኤል ካስተላለፈው መልእክት ጋር መያያዙን ተመልክተናል፡፡ ኢየሱስ በፍፁም መታዘዙ አዳምና እስራኤል ያልቻሉትን እርሱ ግን ፈጽሞታል፡፡ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ትዕዛዛት ታማኝ ነበር፡፡ በሉቃስ ምዕራፍ 23 ቁጥር 43 ኢየሱስ እነዚያን የታወቁ ቃላት የተናገረው ለዚህ ነበር፡፡ እስራኤል በምድረበዳ የተፈተነችው ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት ዝግጁ እንድትሆን ለማድረግ እንደነበረ ሁሉ፣ ሉቃስ ምዕራፍ 23 ቁጥር 43 እንደዘገበው ንስሓ ለገባው ወንበዴም ኢየሱስ እንዲህ ተናግሯል፡

*እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ (ሉቃስ 23፡43)*

የክርስቶስ የጽድቁ ብድራት በገነት የዘላለም ሕይወት ነው፡፡

አዲስ ኪዳን የአዳምንና የሔዋንን፣ ደግሞም የእስራኤልን በምድረበዳ መፈተን፣ ከክርስቶስ ምድራዊ አገልግሎት ከመንግሥቱ ምሥረታ ጋር እንዳዛመደው ተመልክተናል፡፡ ክርስቶስ የመጀመሪያው አዳም የወደቀበትን የፈፀመ ሁለተኛው አዳም ነው፡፡ ክርስቶስ የምድረ በዳ ፈተናውን በድል ተወጣ፣ የእስራኤልንም ውድቀት ቀለበሰ፣ ስለዚህም ወደ ዘላለም ገነት ገባ፡፡

አዲስ ኪዳን አዳምና ሔዋን በገነት የነበሩበትን የሙሴን ዘገባ ከክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት ጋር እንዴት እንዳዛመደው ተመልክተናል፣ ስለዚህ ወደ ሁለተኛው ነጥባችን መሻገር ይገባናል፡፡ አዲስ ኪዳን እነዚህን መርሆች አሁን እኛ በምንኖርበት የመንግሥቱ እድገት ውስጥ እንዴት ያዛምዳቸዋል?

# እድገት

በዚህ ረገድ በርካታ የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ደጋፊ ይሆናሉ፡፡ ሆኖም ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ በእነዚህ የዘፍጥረት ምዕራፎች ላይ የሰጠውን ትኩረት እና ሁለተኛ ያዕቆብ ስለ እነዚህ ጉዳዮች የጻፈበትን መንገድ እንቃኛለን፡፡

## ጳውሎስ

አስቀድመን ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ ምዕራፍ 11 ቁጥር 3 የተናገረውን እንመልከት፡

> *ነገር ግን እባብ በተንኮሉ ሔዋንን እንዳሳታት፣ አሳባችሁ ተበላሽቶ ለክርስቶስ ከሚሆን ቅንነትና ንጽሕና ምናልባት እንዳይለወጥ ብዬ እፈራለሁ፡፡ (2ኛ ቆሮ 11፡3)*

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ጳውሎስ በመቀጠል፣ የቆሮንቶስ ሰዎች ወደ ሌላ ወንጌል ዘወር እንዳይሉ እንደሚሰጋ ያብራራል፡፡ በዚህ ስፍራ ጳውሎስ የሔዋንን አስከፊ ያለመታዘዝ አሉታዊ ተምሳሌት በማንሳት ስለ አስከፊው አለመታዘዝ ማለትም ከክርስቶስ እውነተኛ ወንጌል ዘወር ስለ ማለት ያስጠነቅቃል፡፡ ልክ ሙሴ የሔዋንን መፈተን እስራኤልን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በታማኝነት እንዲጓዙ ለማስጠንቀቅ እንደተጠቀመበት ሁሉ፣ ጳውሎስ ክርስቶስን የሚከተሉ በእርሱ ዘመን የሚኖሩ አማኞች ሁሉ ስለሚጠበቅባቸው መሠረታዊ ታማኝነት ለማስጠንቀቅ ተመሳሳይ ታሪክ ይጠቀማል፡፡ በመንግሥቱ እድገት ወቅት በምትታየዋ ቤተክርስቲያን የሚገኙ በርካታ ሰዎች ከወንጌል መሠረታዊ እውነት ፈቀቅ ከማለት አደጋ ጋር ይጋፈጣሉ፡፡ ቤተክርስቲያን ይህንን የከፋ ክህደት መከላከል ይገባታል ምክንያቱም መዘዙ በአዳምና በሔዋን እንደሆነው ሁሉ እጅግ አሰቃቂ ይሆናልና፡፡

## ያዕቆብ

ያዕቆብም በክርስቲያን ሕይወት ውስጥ የሚገጥሙ ፈተናዎችንና መከራዎችን ሲጠቅስ ከጳውሎስ ጋር ተመሳሳይ አቋም ይይዛል፡፡ በያዕቆብ ምዕራፍ 1 ከቁጥር 12 እስከ 15 እንዲህ እናነብባለን፡

> *በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ከተፈተነ በኋላ ለሚወዱት ተስፋ ስለ እርሱ የሰጣቸውን የሕይወትን አክሊል ይቀበላልና፡፡ … ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ምኞት ሲሳብና ሲታለል ይፈተናል፡፡ ከዚህ በኋላ ምኞት ፅንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች፤ ኃጢአትም ካደገች በኋላ ሞትን ትወልዳለች፡፡ (ያዕቆብ 1 ፡12 -15)*

ያዕቆብ ዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 እያጣቀሰ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በምዕራፍ 1 ቁጥር 14 ውስጥ በሰው "ምኞት" ላይ ያተኩራል፣ ያንንም ኃጢአትን ለማድረግ ከጀርባ እንደሚገፋፋ ኃይል አድርጎ ይጠቅሰዋል፡፡ ሔዋን መልካምንና ክፉን ለምታስታወቀው ዛፍ የነበራት ምኞት ወደ ኃጢአት ገፋፍቷታል፡፡ ሁለተኛ፣ ፈተናውን የሚያልፉ ግን "የሕይወትን አክሊል እንደሚቀበሉ" ያዕቆብ ያብራራል፣ በተቃራኒው የኃጢአት ውጤት ግን "ሞት" ነው፡፡ በሞትና በሕይወት መካከል በዚህ ስፍራ የተቀመጠው ንፅፅር በአዳምና ሔዋን ታሪክ ውስጥ ከተጠቀሰው ጋር ተዳኝ ነው፡፡

እስራኤል በምድረ በዳ በምትፈተንበት ወቅት ሙሴ የአዳምንና የሔዋንን ፈተና በማመልከት በታማኝነት እንድትዘልቅ እንዳበረታታ ሁሉ፣ ጳውሎስና ያዕቆብም በመንግሥቱ እድገት ወቅት

እኛንም በሚገጥመን ፈተና በታማኝነት እንድንፀና ያበረታቱናል፡፡ በክርስትና ሕይወት የሚገጥመን ፈተና እውነተኛ ባህርያችንን ይገልጣል ለዘላለምም ሕይወት ያዘጋጀናል፡፡ በእግዚአብሔር ጸጋ ለክርስቶስ ታማኝ ሆነን ለመዝለቅ የምንችለውን ሁሉ ማድረግ ይገባናል ያን ጊዜም በገነት የዘላለም ሕይወት ብድራት በክብር ይጠብቀናል፡፡

አዳምና ሔዋን በዔድን የነበራቸውን ታሪክ አዲስ ኪዳን በመንግሥቱ ጅማሬና እድገት ውስጥ እንዴት እንደሚያዛምደው ካየን፣ ትኩረታችንን ወደ መጨረሻው እርከን ዘወር ማድረግ ይገባናል፣ ያም በእርሱ ዳግም መምጣት የሚከናወነው የድነት ፍፃሜ ነው፡፡

## ፍፃሜ

ይህም መሪ ሃሳብ በአዲስ ኪዳን በብዙ ስፍራዎች ይገኛል፣ ሆኖም ሁለት ምንባቦችን ብቻ እንዳስሳለን፣ አንዱ በሮሜ ውስጥ ሲሆን ሌላው ደግሞ በራዕይ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል፡፡

## ሮሜ

በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ ለሮሜ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ መደምደሚያ ላይ በሮም ለሚገኙ አማኞች ተስፋን እንዴት እንደሰጣቸው አድምጡ፡፡ በሮሜ ምዕራፍ 16 ቁጥር 20 ውስጥ እንዲህ ጽፏል፡-

> *የሰላምም አምላክ ሰይጣንን ከእግራችሁ በታች ፈጥኖ ይቀጠቅጠዋል፡፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋ ከእናንተ ጋር ይሁን፡፡ (ሮሜ 16፡20)*

በእነዚህ ቃላት፣ በክርስቶስ ዳግም ምፅዓት ወቅት የሮሜ ክርስቲያኖች ስለሚጠብቃቸው ተስፋ ጳውሎስ ያሳስባቸዋል፡፡ ይህንን የሚያደርገው ግን በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ወደ ተሰጠው የድነት ተስፋ መለስ ብሎ በማጣቀስ ነው፡፡ በዚህ ትምህርት አስድመን እንዳየነው፣ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ቁጥር 15 ውስጥ አንድ ቀን የሴቲቱ ዘር፣ የሰው ልጅ፣ የሰይጣንን ዘር ጭንቅላት እንደሚቀጠቅጥ ለእባቡ ይነግረዋል፡፡ በዚህ ምንባብ ክርስቶስ ሲመለስ ሰይጣን በአማኞች እግር ስር እንደሚቀጠቀጥ ጳውሎስ ይናገራል፡፡ ክርስቶስ ራሱ ሰይጣንንና ብርቱ ጠላታችንን ሞትን ያጠፋዋል፡፡ ከዚያም ከክርስቶስ ጋር በድልና በክብር እንነግሣለን፡፡

## ራእይ

የዘፍጥረት ምዕራፍ 2 እና 3 መሪ ሃሳቦች ከመንግሥቱ ፍፃሜ ጋር ተያይዘው የተጠቀሱበት የአዲስ ኪዳን ሌላ ስፍራ የራእይ መጽሐፍ ነው፡፡ ዮሐንስ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሕይወትን ዛፍ ደጋግሞ ጠቅሷል፡፡ በራዕይ ምዕራፍ 2 ቁጥር 7 ጉዳዩን እንዴት እንዳስቀመጠው አድምጡ፡

> *መንፈስ ለአብያተክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ፡፡ ድል ለነሣው በእግዚአብሔር ገነት ካለው ከሕይወት ዛፍ እንዲበላ እሰጠዋለሁ፡፡ (ራእይ 2፡7)*

በዚህ ስፍራ ዘፍጥረት ምዕራፍ 3 የተጠቀሰው በግልፅ ነው፡፡ አዳምና ሔዋን ከዔድን ገነት የተባረሩት እነርሱን ከሕይወት ዛፍ ለማራቅ ነው፡፡ ሆኖም፣ ክርስቶስ ሲመለስ ግን ከሕይወት ዛፍ ይበሉ ዘንድ እግዚአብሔር ለህዝቡ የእንደገና ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ዛፍ የት እንደሚገኝ ልብ በሉ፡፡ ዮሐንስ በግልጥ “በእግዚአብሔር ገነት” በማለት ይናገራል፡፡ ልክ ሙሴ እስራኤል ወደ

ከነዓን እና በዚያም ወደሚገኘው ረጅም ዕድሜ እንድትገባ ጥሪ እንዳደረገ ሁሉ፣ ክርስቲያኖችም እጅግ ይበልጥ በሙላት ወደ ተዘጋጀችው ገነት ሲገቡ፣ የተስፋቸውን ፍፃሜ ይጨብጣሉ፡፡

በሦስተኛ ደረጃ፣ ከዛፉ እንዲበሉ ከተፈቀደላቸው አንፃር ከዘፍጥረት ጋር ያለውን ትስስር እንመለከታለን፡፡ መብቱ የተሰጠው "ድል ለነሣው" መሆኑን ዮሐንስ ይናገራል፡፡ ልክ ሙሴ ለእግዚአብሔር ታማኝ እንድትሆን ለማበረታታት ስለ ሕይወት ዛፍ እንደተናገረ ሁሉ፣ ዮሐንስም በታማኝነት በመዝለቅ ኃጢአትን ድል የነሣ እርሱ ከሕይወት ዛፍ የመብላት ዕድል እንደሚሰጠው ያብራራል፡፡

በመጨረሻ፣ ራእይ ምዕራፍ 22 ቁጥር 1 እና 2 ልንመለከት ይገባናል፡፡ ዮሐንስ አዲሲቷን ምድር በሩቅ በማየት፣ እንዲህ ይናገራል፡-

> *በአደባባይዋም መካከል ከእግዚአብሔርና ከበጉ ዙፋን የሚወጣውን እንደ ብርሌ የሚያንጸባርቀውን የሕይወትን ውኃ ወንዝ አሳየኝ፡፡ በወንዙም ወዲያና ወዲህ በየወሩ እያፈራ ዐሥራ ሁለት ፍሬ የሚሰጥ የሕይወት ዛፍ ነበረ፣ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ፡፡ (ራእይ 22፡1-2)*

የአዲስ ኪዳን አተያይ ግልፅ ነው፡፡ ክርስቶስ መንግሥቱን ወደ ፍፃሜ ለማምጣት ሲመለስ፣ በክርስቶስ የታመኑ ወደ ዔድን ገነት ይገባሉ፡፡ ሰይጣን ከእግራችን በታች ይቀጠቀጣል እኛም ከሕይወት ዛፍ እንበላለን እግዚአብሔር ባዘጋጀው አዲስ ስፍራም ለዘላለም እንኖራለን፡፡

## ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት ሙሴ አዳምና ሔዋን በገነት ስለ ነበሩበት ሁኔታ የጻፈው እስራኤላውያን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በሚያደርጉት ጉዞ ሊያግዛቸው እንደሆነ ተመልክተናል፡፡ በዔድን ገነት የሆነውን ነገር እንዲቀለብሱ ለእስራኤል ጥሪ አቅርቧል፡፡ በብዙ ገጽታዎች የዚህ ምንባብ መልእክት ዛሬም ለእኛ በጣም ተመሳሳይ ነው፡፡ እስራኤል ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንድትገፋ ሙሴ ያቀረበውን ጥሪ በመስማት፣ እኛም የአዳምንና የሔዋንን መንገዶች እንዴት መቀልበስ እንዳለብን እንመለከታለን፡፡ በክርስቶስ በማመንና በታማኝነት በመዝለቅ ጠፍቶ በተገኘው ገነት መዳንን እንወርሳለን፡፡